የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## የሕዝብ ትግል በጭፍን ሽብር አይገታም

ሰኔ ፩ የሰው ደም እንደጎርፍ የፈሰሰበትንና ከፍተኛና አሰቃቂ ሽብር የተካሄደበትን የሀዘን ቀን የሚያስታውሰን ቀን ነው ፡፡ ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም በአሸባሪው የመለሰ መንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ሕይታቸውን ያጡትን፥ አካለ ጎደሎ የሆኑንትን፥ በገፍ የታሠሩትን የተጋዙትን ወገኖቻችንን ስናስታወስ በከፍተኛ ሀዘን ነው፡፡

ላለፉት ፲፬ ዓመታት በጠመንጃ አፈሙዝ ሥልጣን በጨበጠ ኃይል በደልና ስቃይ ሲደርስበት የቆየው የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. በነቂስ ወጥቶ ይኽ አገዛዝ ለአንዴም ለሁሌም እንዲያበቃ በድምፁ ውሳኔ መስጠቱ እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን ምርጫውን ለመታዘብ የመጡት የዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ያረጋገጡት ሐቅ ነው፡፡ ከሥልጣኑ በስተቀር ለሕዝብ መብትም ሆነ ለአገር ደኅንነት ደንታ የሌለው ሕወሓት/ኢሕዴግ የድምፅ ቆጠራውን በማጭበርበርና የሕዝብን ድምፅ በመስረቅ ምርጫውን አሸንፌያለሁ ብሎ በማን አለብኝነት በሥልጣን ለመቆየት ያደረገው ውሳኔ ሕዝባችንን ከዳር አስከዳር አስቆጥቶታል፥ አሳዝንኖታል፥ መብቱን ለማስከበርና ድምፁን ለማስመለስ ይበልጥ እንዲቆርጥ፥ እንዲወስን እንዲነሳሳ አድርጎታል፡፡

በሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የሕዝብ ድምፅ ይከበር፥ የሕዝብ መብት ይጠበቅ፥ የሥልጣን ምንጭ የመሣሪያ አፈሙዝ ሳይሆን ሕዝብ መሆኑ ይረጋገጥ ፥ የሕዝባችን ድምፅ አይሰረቅ በማለት ኢትዮጵያውያን በተለይም ተማሪዎችና ወጣቶች በሰለማዊ መንገድ ላቀረቡት ጥያቄና ላካሄዱት ሰላማዊ ትግል አገዛዙ የሰጣቸው መልስ የጥይት እሩምታና አሰቃዊ የሽብር ተግባራት ነበር፡፡ በመሆኑም በዚች ቀን በርካታ ወጎኖቻችን ሕይዎታቸውን አጥተዋል፥ በተተኮሱ ጥይቶች አካለ ስንኩሎች ሆነዋል፥ ብዙዎቹ ወደ አስር ቤት ተወርውረዋል፥ ሰቆቃዊ ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል፥ ቤት ንብረታቸው ወድሟል፥ ቤተሰቦቻቸውንም አጥተዋል፥ የተወሰኑትም የሚወዷት አገራቸውን ጥለው ተሰደዋል፡፡

ሕዝባችን የተሰረቀ ድምፁን ለማስመለስ፥ የመብቱ ባለቤት ለመሆን ያካሄደው መራራ ትግልም ሆነ በአሸባሪው መንግሥት የተሰነዘረበት የሽበር እርምጃ በሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም አላበቃም፡፡ በተከታታይ ጊዜያት ሕዘባችን ለመብቱ መከበር ያደረጋቸው ትግሎች በተጠናከሩና በተስፋፉ ሽብሮች ለመግታት ተሞክሯል፡፡ በመስከረም ፲፱፻፺፰ የተካሄደው እልቂት፥ በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ከተሞችና ገጠሮች ላይ የአገዛዙ የፀጥታ ኃይሎች ያካሄዷቸው ጭፍን ግድያዎች፥ በፖለቲካ ድርጅቶች፥ በሲቪክና የሙያ ማኅበራት መሪዎች፥ በወጣቶችና አዛውንት፥ ምግባረ-ሰናይ ድርጅት መሪዎችና አባላት ላይ የተካሄዱት የጅምላ እስራቶች፥ የአገዛዙን አረመኔያዊ የሽበር እርምጃዎችንና አስከፊ ባህሪዎችን የሚገልጹ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

የግንቦቱ ምርጫ የአገዛዙን ማንነት እና ምንነት በገሃድ አጋለጠ እንጂ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በ ፲፬ ዓመታት የሥልጣን ዘመኑ ከሽበር እርምጃዎች የተለየበት ጊዜ አልነበረም፡፡ በ ፲፱፻፹፬ እና በ ፲፱፻፺፬ ዓ/ም በተማሪዎች ላይ ያካሄዳቸው ጭፍን ግድያዎች፥ በተለያዩ ጊዜያት በገጠርና በከተማ ያደረጋቸው ግድያዎች ይኽ አገዛዝ ለሰው ልጅ ሕይዎት ደንታ የሌለው መሆኑን በገሃድ ያሳያል፡፡ ለሕዝብ መብት መረጋገጥ፥ ለድምፁ መከበር ሲሉ ሕይዎታቸውን

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

መስዋዕት ያደረጉ ወጎኖች ምን ጊዜም ኅያው ናቸው:: ለተቀደሰ ዓላማ ሲዋደቁ አካላቸው የጎደለውም ሆነ በየእስር ቤቱ በስቃይ የሚማቅቁ ወጎኖች ምን ጊዜም የማይረሱ የአገሪቱ ውድ ዜጎች ናቸው::

የሰውን መብት እያፈኑ፥ እየገደሉና እየጨፈጨፉ ዘለዓለም በሥልጣን ላይ መቆየት እንደማይቻል እነ አቶ መለስ ዜናዊ ሊረዱት ያልቻሉት ሐቅ ነው:: አምባገን ኃይሎች የመሣሪያ ክምችታቸውንም ሆነ የተባባሪዎቻቸውን ድጋፍ ተገን በማድረግ ለተወሰነ ጊዜ በሥልጣን ላይ መቆየት ቢችሉም በሕዝብ ኃይልና ትግል እየተንኮታኮቱ የማታ ማታ ወደ መቃብር መውረዳቸው በአገራችንም ሆነ በሌሎች ሕዝቦች ታሪክ የተዘገበ ሐቅ ነው::

የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነን መንግሥት ምንም እንኳ የሽበር ተግባሮችን አስፋፍቶና አጠናክሮ ቢቀጥልም፥ ቀደም ብለው የነበሩት መብቶች ጭራሽ ተሰርዘው አምባገነን አገዛዝ ቢነግስም፥ በአገሪቱ ኤኮኖሚ መንኮታኮትና በድህነት መስፋፋት ምክንያት ሕዝቡ ከፍተኛ ስቃይው ውስጥ እንዲገኝ ቢደረግም፥ ሕዝባዊው ትግል አሁንም ኅያው ሆኖ እየቀጠለ ነው:: የሕዝቡ ቁጣ አልበረደም፥ የትግል ስሜቱም አልቀዘቀዘም:: የአረመኔያዊ አገዛዝ የሽብር፥ የአፈናና የጭፍጨፋ ተግባሮች የሕዝባችንን ትግል አላደከሙትም፥ አላኮሰመኑትም፥ ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አደረጉት እንጂ::

የሕዝብ ትግል ተጠናክሮ ግቡን የሚመታው ሕዝባችን የሥልጣን ምንጭ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው:: የሰኔ አንዱን አረመኔያዊ ድርጊት በሀዘን ስናከብር በጥሞና ማስተዋል ያለብን ጉዳይ ይኸ የሕዝብ ትግል ተጠናክሮ ግቡን እንዲመታ የማድረጉ ኃላፊነት በሁላችንም ላይ የወደቀ መሆኑን ነው::

ከአገራችን አምባገነን ሥርዓትን ለአንዴም ለሁሌም ለማስወገድና በሰከነ፥ መሠረቱ በሰፋና በተጠናከረ የሽግግር ሂደት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን የሚሆንበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሕዝብ ትግልና ተሳትፎ ወሳኝ ነው:: ይኸን የሕዝብ ትግል አቅጣጫ ለመስጠት ለመምራትና ለማስተባበር በተለይም የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክ ማኅበራትና ሌሎች የተደራጁ ክፍሎች የተለየ ኃላፊነት ስላለብን ይኸን እውን ለማድረግ ሁላችንም እንረባረብ እንላለን::

ሰማዕቶቻችን ለወደቁበት ዓላማ እውንነት የጋራው ትግል ይቀጥል!
የጠራ ዓላማ፥ ትክክለኛ አቅጣጫና አመራር ያለው የሕዝብ ትግል ምን ጊዜም አሸናፊ ነው!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት

ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.